# ዝባድ!



ዝባድ ላቧን፣ ወዝዋን በዕንጨት፣ በጋሬጣ
ወይ በሾለ ዲንጋይ ኣስጠግታ፣ ኣፍርጣ
ቆሻሻ ሆኖባት፣ ግማት፣ ጭቅቅት
ጠርጋ ታብሳለች ለመጸዳጀት…

ሰውም ላቧን ወስዶ፣ ኣንጥሮና ኣፍልቶ
በጥበብ፣ ብልሓት ይሠራዋል ሽቶ
ጠረኗ ደስ ይላል፣ ከሩቅም ያውዳል
ላቧም የወርቅ ያህል እጅግ ይወደዳል!





ዝባድ በሌላ ስም ይሏታል ጥሪኝ
ግን እርሷ ኣትጣራም፣ ምን ብትሆን ሞኝ
ወዝዋ ከሸተተው ኣይቀርባት ትንኝ
ለሌላም ፈውስ ናት ሲሉ ሰማሁኝ



ለፍታ፣ ወጥታ፣ ወርዳ፣ በላብዋ ድካም
በማደን ስትኖር ቀላል ኣይደለም!
ትላ-ትል፣ ገበሎ፣ ኣይጥ፣ እንሽላሊት
ቀለቧ ነው ኣሉ ቀንድ-ኣውጣ፣ ዕንቁራሪት

በብላሽ ኣይሰጥም የሰው ልጅ ዓቅሙን
ዋጋ ሳያስከፍል የላብ፣ ደም-ወዙን
ይህን ብታውቅ ዝባድ መች እንዲህ በቀላል
ላቧን ትሰጥ ነበር ሳትል፣ "ይከፈላል!"

ገ/ኢ.. ጐርፉ።